አዋጅ ቁጥር ----------/2009

# የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለውን ልዩ ጥቅም ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49(5) የኦሮሚያ ክልል የአገልግሎት አቅርቦት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ፣ እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም እንደሚጠበቅለት የደነገገ በመሆኑ፤

የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለውን ልዩ ጥቅም በሕግ መወሰን እንዳለበት ሕገ-መንግሥቱ ስለሚደነግግና ለዚህም ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለውን ልዩ ጥቅም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ------/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1/ “ሕገ-መንግሥት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፤

2/ “አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

3/ “ክልል” ማለት የኦሮሚያ ክልል ነው፤

4/ “ልዩ ጥቅም” ማለት በሕገ መንግሥቱ እውቅና ያገኙ የአገልግሎት አቅርቦት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉት፣ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ናቸው፤

5/ “የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ እና ዙሪያው ነዋሪ የሆኑ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችን በሙሉ ያካትታል፤

6/ “የአዲስ አበባ ከተማ ወሰን” ማለት የከተማው አስተዳድር ከኦሮሚያ ክልል ጋር በሚያደርገው ስምምነት ተወስኖ ምልክት የተደረገበት ወሰን ነው፤

7/ “የአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ” ማለት ፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ነው፤

8/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በአዲስ አበባ ከተማ ወሰን ውስጥ እና እንደአግባቡ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

# <u>ክፍል ሁለት</u>
# <u>ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው የማህበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ልዩ ጥቅም</u>

## 4. <u>የትምህርት አገልግሎት</u>

በአስተዳድሩ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች በአፋን ኦሮሞ የሚማሩበት ትምህርት ተቋማት በከተማ አስተዳድሩ ወጪ እንዲደራጁ ይደረጋል።

## 5. <u>የጤና አገልግሎት</u>

በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ባሉ ከተሞችና ገጠሮች የሚኖሩ ነዋሪዎች በከተማው ውስጥ በሚገኙ የመንግሥት ሆስፒታሎች እና ጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንደማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ እንዲያገኙ ይደረጋል።

## 6. <u>ባሕል፣ ቋንቋና ሥነጥበብ አገልግሎቶች</u>

1/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ልዩ ጥቅም አገልግሎቶችን ለኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ለማቅረብ እንዲቻል አፋን ኦሮሞ በከተማ አስተዳደሩ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል።

2/ የኦሮሞ ሕዝብ ማንነት የሚያንፀባርቅ አሻራ በከተማው ውስጥ በቋሚነት እንዲኖር ከክልሉ ሕዝብ ጋር በተያያዙ ታሪካዊ ክስተቶች ስም መታሰቢያዎች እንዲኖሩ አመቺ የሆኑ እንደ አደባባዮች፣ ጎዳናዎች፣ ሠፈሮች እና የመሳሰሉት ቦታዎች እንደአስፈላጊነቱ በቀድሞ የኦሮሞ ስማቸው እንዲጠሩ ይደረጋል።

DRAFT

3/ በከተማው አስተዳድር የኦሮሞ ሕዝብ ባህልና ታሪክ የሚያንጸባርቁ ቲያትር ቤቶች፣ የመዝናኛ፣ የባሕል እና የኪነጥበብ ማዕከሎች የሚገነቡበትንና የሚተዋዉቁበት ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል፡፡

4/ በከተማው አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ ሙዚየሞች ውስጥ የኦሮሞን ሕዝብ ታሪክ፣ ባሕልና ወግ የሚያንጸባርቁ ቅርሶችና መጽሐፎች እንዲሟሉና እንዲኖሩ አስተዳድሩ ከክልሉ ጋር በመመካከር ይሠራል፡፡

5/ በከተማዋ በመንግሥት የሚሰራጩ የመገናኛ ብዙሃን በአፋን ኦሮሞ ጭምር የሚጠቀሙበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

6/ ከኦሮሚያ ክልል ጋር በተያያዘ ከተማው የተቆረቆረበት በአፋን ኦሮሞ የቀድሞ ስሙ ፊንፊኔ አዲስ አበባ ከሚለው የከተማው መጠሪያ ጋር በሕግ ፊት እኩል እውቅና ይኖረዋል፤ የስሞቹን አጠቃቀም በተመለከተ በደንብ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ልዩ ጥቅም</u>

7. ***<u>መሬት አቅርቦት</u>***

ክልሉ ለተለያዩ መንግስታዊ ሥራዎች እና ሕዝባዊ አገልግሎቶች የሚውሉ ሕንፃዎች የሚሠሩበትን መሬት ከሊዝ ነጻ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

8. ***<u>የውኃ አቅርቦት</u>***

የከተማው አስተዳደር ከክልሉ ከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የሚያገኘው የመጠጥ ውኃ ምንጭ ጉድጓድ የሚቆፈርበት፣ ግድቡ የሚለማበት፣ ወይም የውኃ መስመሩ አቋርጦ የሚያልፍባቸው የክልሉ ከተሞች እና ቀበሌዎች በአስተዳደሩ ወጪ የመጠጥ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

9. ***<u>የትራንስፖርት አገልግሎት</u>***

የከተማ አውቶቡስና ታክሲዎች ትራንስፖርት ስምሪት እንዲሁም የባቡር መሠረተ ልማት ዝርጋታና አገልገሎት በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያሉትን የክልሉ ከተሞች ያማከለ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

10. ***<u>የሥራ ዕድል</u>***

1/ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ የክልሉ ከተሞችና ገጠሮች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ወጣቶች በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

2/ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ የክልሉ ከተሞችና ገጠሮች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ወጣቶች ከውኃ ልማት፣ ከደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ ከቆሻሻ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ከተፋሰስ ልማት፣ ከትራንስፖርት አገልግሎት እና ከመሳሰሉት ጋር ተያይዞ የሚመነጭ ሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

11. <u>የገበያ ቦታ አቅርቦት</u>

1/ የክልሉ አርሶ አደሮች በተደራጀ መልኩ ምርቶቻቸውን የሚሸጡበት የገበያ ቦታ ይደራጅላቸዋል፡፡

2/ የከተማ አስተዳደሩ በራሱ ወጪ የገበያ ቦታውን ገንብቶ ለግብይት ሥራ ምቹ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

12. <u>የኮንዶሚኒየም ቤት ተጠቃሚነት</u>

በመንግሥት ወጪ ከሚገነቡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ሠራተኞችና ኃላፊዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ኮታ ተሰጥቷቸው በዕጣ ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

13. <u>ካሣ የማግኘት እና በዘላቂነት የመቋቋም</u>

1/ በአስተዳድሩ ውስጥ በልማት ምክንያት የሚፈናቀሉ አርሶ አደሮች ዘላቂ መቋቋሚያ የሚሆን ካሣ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል፡፡

2/ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ከዚህ በፊት በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ እና በቂ ካሣ ያላገኙ አርሶ አደሮች በጥናት ላይ የተመሠረተ የማቋቋሚያ ሥራ እንዲሰራላቸው ይደረጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጾች (1) እና (2) የተመለከቱትን ጉዳዮች የሚመራ ራሱን የቻለ ጽሕፈት ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የአካባቢ ጥበቃ ልዩ ጥቅም</u>

14. <u>የተፋሰስ ልማት</u>

ለከተማው አስተዳድር የመጠጥ ውኃ አቀርቦት የውኃ ምንጭ የተቆፈረበት፣ ግድብ የለማበት፣ ወይም የውኃ መስመር አቋርጦ የሚያልፍባቸው የክልሉ ከተሞች እና ቀበሌዎች በአስተዳድሩ ወጪ የተፋሰስ ልማት የሚያካሂዱበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 15. ከአካባቢ ብክለት የመጠበቅ መብት

1/ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያሉ ከተሞችና ቀበሌዎች ከከተማው ከሚወጡ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከሚደርሱ የአካባቢ ብክለትና ጉዳት የመጠበቅ መብት ይኖራቸዋል፡፡

2/ ከአዲስ አበባ ከተማ በሚወጡ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከሚደርሱ የአካባቢ ብክለትና ጉዳት የክልሉን ከተሞችና ቀበሌዎች ለመጠበቅ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲካሄድ ይደረጋል፤ በግምገማው መሠረት አስፈላጊው የማስተካከያዎች ይደረጋሉ፡፡

3/ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያሉ ከተሞችና ቀበሌዎች ደህንነቱ ሳይጠበቅና ቁጥጥር ሳይደረግበት ከተቀመጠው ደረጃ በላይ ወደ ክልሉ በተጣሉ ወይም በፈሰሱ ቆሻሻዎች ምክንያት በሰው፣ በእንስሳትና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት በሕግ አግባብ ከአስተዳድሩ ካሳ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል፡፡

4/ ለአዲስ አበባ ከተማ ልማት የሚውሉ የግንባታ ማዕድናት ማግኛ ሥፍራዎች የአየር ብክለት እንዳያስከትሉ እና ለደን ልማት ወይም ለሌሎች ልማቶች መዋል እንዲችሉ እንዲያገግሙ ይደረጋል፡፡

5/ ለአዲስ አበባ ከተማ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያና ማስወገጃ ቦታዎች እንዲሁም መልሶ መጠቀሚያ ስፍራዎች አስተዳድሩና ክልሉ በጋራ ባጠኗቸው ቦታዎችና ሳይንሳዊ መስፈርቶችን ባሟሉ ሁኔታዎች እንዲተዳደሩ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለጋራ ምክር ቤት

## 16. የጋራ ምክር ቤት መቋቋም

1/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱትንና ሌሎች የጋራ ጉዳዮችን ክልሉ እና አስተዳድሩ የሚወያዩበትና የሚወስኑበት የጋራ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" ተብሎ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለፌዴራል መንግሥት ይሆናል፡፡

## 17. የምክር ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት

የምክር ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ነው፡፡

## 18. የምክር ቤቱ ዓላማ

የምክር ቤቱ ዓላማ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 49(5) መሠረት የኦሮሚያ ክልል የአገልግሎት አቅርቦት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉትን ጉዳዮች

በተመለከተ፣ እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩት ልዩ ጥቅሞች በተጨባጭ ተግባራዊ እንዲሆን መከታተል፣ መገምገምና ለአፈጻጸሙ ቅልጥፍና ድጋፍ ማድረግ ይሆናል፡፡

19. **<u>የምክር ቤቱ አባላት</u>**

የምክር ቤቱ አባላት ከአስተዳድሩ ምክር ቤትና ከክልሉ ምክር ቤት በእኩል ቁጥር የሚወከሉ ይሆናል፡፡

20. **<u>የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የምክር ቤቱ አወቃቀር፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ የሥራ ዘመን፣ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት፣ የአባላት ሥነ-ምግባር እና በጀት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

21. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችንና ምክር ቤቱ የሚያወጣውን መመሪያና ውሳኔዎች ሥራ ላይ ለማዋል ማንኛውም ሰው ወይም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

22. **<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ይህን አዋጅ የሚቃረን አዋጅ ወይም ውሳኔ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

23. **<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ምክር ቤቱ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

24. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ………………..2009 ዓ.ም

ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

DRAFT